*በ ዩናይትድ ስቴትስ  የዓለም አቀፍ ኃይማኖታዊ ነጻነት ኮሚሽን (ተልዕኮ) (The U.S. Commission on International Religious Freedom) (ወይም በእንግሊዝኛው ምህጻረ-ቃል«USCIRF») ከስቴት ዲፓርትመንት (ከአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር) የተለየና ራሱን የቻለ አካል ነው።   በአሜሪካ ኮንግረስ የተፈጠረ፣ ገለልተኛ፣ የሁለቱም የፖለቲካ ፓርቲዎች ትብብር የሚታይበት፣ ዓለም አቀፍ የሆነ ኃይማኖታዊ ነጻነትን አስመልክቶ ጥናትን በማካሄድ (በአጽንዖት በመከታተል)፣ ለፕሬዝዳንቱ፣ ለውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ እና ለ ኮንግረስ (ለአሜሪካ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት)፣ መተዳደሪያ ደንብ (ፖሊሲን) አስመልክቶ፣ ለአሜሪካ መንግስት አማካሪ አካል ነው።  «USCIRF» እነዚህን ምክሮች የሚያቀርበው በህግ በተሰጠው ተልዕኮ እና በ ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ጥበቃ እንዲሁም በሌሎች ዓለም አቀፋዊ ዶክመንቶች ላይ በመመርኮዝ ነው።  ይህ (እ. ኤ. አ.) የ 2016 ዓ.ም. ሪፖርት/ ዘገባ የሚወክለው፣ በኮሚሽነሮች እና በሰለጠኑ ባለሙያዎች (ፕሮፌሽናሎች)፣ በተጠቀሱት ቦታዎች የሚፈጸሙ ግፎችን/ በደሎችን በመመዝገብ እና ገለልተኛ የሆኑ ምክሮችን/ጥቆማዎችን ለአሜሪካ መንግስት ለመስጠት የተሠራውን ሥራ ነው። የ እ. ኤ. አ. 2016 ሪፖርት/ ዘገባ የሚሸፍነው ወቅት ከ ፌብሩዋሪ 1/ 2015 ዓ.ም. እስከ ፌብሩዋሪ 29/ 2016 ዓ.ም. ድረስ ያለውን ጊዜ ሲሆን፣ ሆንም ግን፣  በአንዳንድ ጉዳዮች፣ ከዚህ ወቅት በኋላ የተከሰቱ ሁኔታዎችም ተጠቅሰዋል።*

# የአፍሪካ ቀንድ

በአፍሪካ ቀንድ ክልል የኃይማኖታዊ ነጻነት ጥሰቶች በጣም በዝተው ይታያሉ።     በዚህ ሪፖርት/ዘገባ ከዚህ ቀደም እንደተጠቀሰው ሁሉ፣  «USCIRF» ቀጣይነት ባለው ሁኔታ አሁንም ኤርትራና ሱዳን be መንግስቶቻቸው ከሚፈጽሙት የተቀናጀ፣ ቀጣይነት ያለው፣ እና አስደንጋጭ የሆነ/ዓይን ያወጣ ኃይማኖታዊ ነጻነት ጥሰቶች የተነሳ፣ «ልዩ ትኩረት የሚያስፈልጋቸው ሀገራት» (በእንግሊዝኛ ምህጻረ-ቃሉም «CPC») ተብለው እንዲመደቡ ምክሩን መስጠቱን/ጥቆማ ማድረጉን ይቀጥላል። በተጨማሪም፣ ኢትዮጵያ፣ ኬንያ፣ እና ሶማሊያ ደግመው   በኃይማኖታዊ ነጻነት ጥሰቶች ይታወካሉ። በአሜሪካ መንግስትአሸባሪ ተብሎ የተመደበውአል ሻባብ   በኬንያና በሶማሊያ ውስጥ ለተፈጸሙት በዛት ያላቸው ግፎች ተጠያቂ ነው።  ሆኖም ለሽብርተኝነት እና ኃይማኖታዊ አክራሪነት የኢትዮጵያና የኬንያ መንግስታት የሚሰጧቸው ምላሾች በራሳቸው ወደ ኃይማኖታዊ ነጻነት ጥሰት ይመራሉ። በሶማሊያ፣ መንግስታዊና ማህበረሰባዊ የሆኑ ኃይማኖታዊ አለመቻቻሎች፣ ለሀገሪቱ ደካማ ኃይማኖታዊ ነጻነት ሪኮርድ አስተዋጽዖ ያደርጋሉ።

## ሶማሊያ

***መንደርደሪያ/መነሻ፡-*** የሶማሊያ ፌደራል መንግስት፣ በአሁን ወቅት ያለው የሽግግር መንግስት፣ የተመሰረተው እ.ኤ.አ. በ ኦገስት 2012 ዓ.ም. ነው።   እ.ኤ.አ. በ ጃኑዋሪ 2016፣ የሶማሊያ የፖለቲካዊ መሪዎች፣ በ ታቀደው የ እ.ኤ.አ. ኦገስት 2016 ዓ.ም. ምርጫ ወቅት፣ ቋሚ መንግስት ወደ ሥልጣን በምርጫ እንደሚገባ ተስማምተዋል።    በ እ.ኤ.አ. 2015፣ የሽግግር ባለስልጣናት ባለመስማማት/ጥል የተሞላ ጥረታቸውን፣ ፌደራላዊ ሀገርን ለመመስረት  በሚል የቀጠሉ ሲሆን፣ጊዜያዊ አስተዳደ ባለስልጣናትም መስተዳድርን ለመመስረት ይታገላሉ።

***ጊዜያዊ ህገ-መንግስት፡-*** የሶማሌ መንግስት ከኃይማኖታዊ ነጻነት ጋር ተቃራኒ የሆኑ ድንግጋት ያሉበትን የጊዜያዊ ህገ-መንግስት መከለሱን እንደቀጠለ ነው። ህገ-መንግስቱ ኃይማኖታዊ ክህደትን በግል የሚከለክል ሲሆን ቁርዓንን እና ሱናን የሀገሪቱ ዋና የህግ ምንጭ አድርጎ ይሰይማል።

***ማህበረሰባዊና መንግስታዊ አለመቻቻል፡-*** ሶማሌዎችበአብዛኛው ሁሉም የሱኒ እስልምና ተከታዮች ናቸው። ክርስትያኖች በሶማሊያ በቤተሰቦቻቸውና በማህበረሰባቸው ስደት ይደርስባቸዋል። ሶማሌ ኃይማኖታዊ መሪዎች እና አል ሻባብ እንዳሉት፣ ክርስትና፣ ክርስትያኖች እና ቤት ክርስትያኖች ከሶማሊያ ጋር የማይጣጣሙ ናቸው። የሶማሊያ መንግስትም ክርስትያኖችን አስመልክቶ አለምቻቻልን/ሙሉ ተቃውሞን አሳይቷል። በ እ.ኤ.አ. 2013 እና 2015 ዓ.ም.፣ የገና በዓልን ስለማክበር አስመልክቶ የመንግስት ባለሥልጣናት ማዕቀብ መጣሉን አውጀው ከዛም በኋላ ማስተባበያ ሰጥተዋል።

በአዲስ ክስተት ደግሞ፣ የሺያ እስልምና ተከታዮች በሶማሊያ የማስፈራሪያ ጥቃት እንደደረሰባቸው በዚህ ሪፖርት ማቅረቢያ ጊዜ ተረጋግጧል። በ እ.ኤ.አ. ዲሴምበር 23፣ሁለት የኢራን ዜጎችን ኃይማኖትን ለማስቀየር ስብከት አድርጋችኋል በሚል ክስ አስረው ከዛም ከሀገር አስወጥተዋቸዋል። በጃንዋሪ 2016፣ የሶማሌ መንግስ ከኢራን ጋር ያለውን ግንኙነት አቋርጧል። በ እ.ኤ.አ. ጃንዋሪ 12፣ የሶማሊላንድ ዳኛሁለት የ ፓኪስታን ዜጎችን የሺያ እስልምናን አስፋፍተዋል በሚል የገንዘብ ቅጣት እና እሥራት ፈርደውባቸዋል።

***አል ሻባብ፡-*** አል ሻባብ (ደግሞም በሌሎች ስሞቹ ሃራካት ሻባብ አል-ሙጃሂዲን፣ ሻባብ፣ ሙጃሂዲን አል-ሻባብ እንቅስቃሴ፣ ሙጃሂዲን ወጣቶች እንቅስቃሴ ተብሎ የሚታወቀው) የእስልምና ፍርድ ቤቶች «UIC» ህብረት የወታደራዊ ክንፍ/ቅርንጫፍ በመሆን ወደ መታወቅ ደረሰ። የተጠቀሱ ግቦቹም ሶማሊያን በእስላማዊ ህግጋት የምትተዳደር ሀገር ማድረግ፣ በጎረቤት ሀገራት የሚገኙ በዘር ሶማሌ የሆኑ ህዝቦች የሚገኙባቸውን ቦታዎችን ጨምሮ ታላቅ ሶማሊያን መገንባት እና እጅግ በጣም የጠበቀ/የከረረ እስልምናን ማስፋፋት ናቸው። እ.ኤ.አ. ከ 2007 ዓ.ም. ጀምሮ አል-ሻባብ ሶማሊያን ለመቆጣጠር ካለው ዘመቻ ተያይዞ፣ የሶማሌ እና ክልላዊ የሆኑ ኃይላትን ሲዋጋ ቆይቷል፤ አንዳንድ ጊዜም በሀገሪቱ የሚገኙ መካከለኛ እና ደቡባዊ ክፍላትን ሰፋፊ ግዛቶች ተቆጣጥሮ ቆይቷል።

እ.ኤ.አ. በ ፌብሩዋሪ 2012 ዓ.ም.፣ ለ አልቃይዳ በመሃላ ታማኝነቱን ገልጿል። እ.ኤ.አ. በ 2015 ዓ.ም. በ አል-ሻባብ ውስጥ ለ አልቃይዳ ካለው ታማኝነት የተነሳ ክፍፍሎች መታየት የጀመሩት ተገንጣይ ቡድኑ ከእስላማዊ ግዛት እና ባህረ ሰላጤ (አይስስ) ጋር ኃይሉን ለማቀናጀት በመወሰኑ ምክንያት ነው። እ.ኤ.አ. በ ኦክቶበር 22፣ ከፍተኛ የአልሻባብ መሪ የሆኑት ሼክ አብድርቃድር ሙሚን እና እና ወደ 20 የሚጠጉ ተከታዮቻቸው ከ «ISIL» ጋር ለመተባበር በመሃላ ቃል ገብተዋል። በምላሹም፣ አል-ሻባብ እነዚህን የ «አይስስ» ተከታዮች አስሮ በሞት በምቅጣት ለ አል-ቃይዳ ያለውን ታማኝነት አጽንቷል።

በዚህ የሪፖርት ማቅረቢያ የጊዜ ክፍተት ውስጥ፣ በደቡብ ሶማሊያ ያለው የደህንነት ሁኔታ ከፍተኛ አለመረጋጋት የሚታይበት ሆኖ ቆይቷል። አል-ሻባብ ተደጋጋሚ ጥቃቶችን በሶማሊያ በተሰማራው የአፍሪካ ህብረት ሠራዊት «AMISOM» ላይ፣ በሶማሌ ብሔራዊ ጦር፣ በመካከለኛና ደቡባዊ ሶማሊያ በሚገኙ ሰላማዊ ማህበረሰቦች እንዲሁም አልፎ አልፎ የሚታዩ ጥቃቶችን በራስ-ገዝ በሆነው በፑንትላንድ ክልል ላይ ፈጽሟል። በሞቃድሾ፣ የአል-ሻባብ የቦምብ ፍንዳታዎች የሶማሌ መንግስት ባለሥልጣናትን፣ ዓለም ዓቀፍ ተወካዮችን እና ሶማሌ ሰላማዊ ማህበረሰቡን ገድለዋል። ቡድኑ ከኃዲያን ወይም ኢ-እስላማዊ ያላቸውን የመንግስት ባለስልጣናት እና ተባባሪዎቻቸውን ነፍስ አጥፍቷል። በተጨማሪም፣ አል-ሻባብ ጭካኒያዊ የተሞላ የእስልምና ህግ አተረጓጎምን በኃይል ማስፈጸሙን ክርስትያኖችን እና

«ጥንቁልናን» ፈጽመዋል ትብለው የተከሰሱ ዜጎችን በመግደል ቀጥሏል። በአስገድዶ መድፈር እና መወስለት የተከሰሱ ግለሰቦችንም በግርፋት ቀጥቷል።

# ኬንያ

***መንደርደሪያ:-*** የኬንያ ህገ-መንግስት እና ሌሎች ህግጋት ለኃይማኖታዊ ነጻነት ከለላ ይሰጣሉ፣ ጨምሮም በአምልኮ፣ በማክበር፣ በማስተማር፣ እና በመከተል ነጻነትን እንዲሁም ኃይማኖታዊ መድልዎን ፈጽሞ ይከለክላሉ። ነገር ግን፣ ለአል-ሻባብ መንግስት የሰጣቸው ምላሾች፣ ውጤታቸው ሰፊ የሆነ የጅምላ ቅጣት በሱማሌ ዜጎች እና በዘር ሱማሌ የሆኑ ሌሎችን ሙስሊሞች ላይ ማድረስ ሆኗል።

***አል-ሻባብ:-*** እ.ኤ.አ. በ 2011 ዓ.ም. ኬንያ፣ አል-ሻባብ በዛች ሀገር ያለውን ግፊት ለመግታት፣ ወታደራዊ ኃይሏን ወደ ሶማሊያ ልካለች። አል-ሻባብም በምላሹጥቃቱን ወደ ኬንያ ውስጥ አስፋፍቷል። ይህም እ.ኤ.አ. የ ሴፕቴምበር 2013 ዓ.ም. «ዌስት ጌት» የገበያ አዳራሽ የሽብር ጥቃትን፣ ከ እ.ኤ.አ. ጁን-ጁላይ 2014 አምስት ሣምንታት የፈጀ ዘመቻን በ «ላሙ» እና «ጣና ወንዝ» ግዛቶች እንዲሁም ብዛት ያላቸው የሽብር ጥቃቶችን በሀገሪቱ ሁሉ አስፋፍቷል። ቡደኑ ሙስሊሞችን እና ሙስሊም ያልሆኑትን ገድሏል፣ ነገር ግን የአል-ሻባብ ሽብርተኞች በጥቃቶቻቸው ሁልጊዜም ክርስትያኖችን ለመለየትና ለማውጣት ይተጋሉ። በዚህ ሪፖርት ማቀናበሪያ ጊዜ፣ በኬንያ ከሁሉም ጎልቶ የሚታየው የ አል-ሻባብ ጥቃት የደረሰው እ.ኤ.አ. በ አፕሪል 2 በ ጋሪሳ ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ ነው፤ እ.ኤ.አ. ከ998 ዓ.ም. የአሜሪካ ኤምባሲ የቦምብ ጥቃት በኋላ እጅግ የከፋ ነው በተባለለት የሽብር ጥቃት፣ 148 ተማሪዎች ተገድለዋል። እ.ኤ.አ. በጁን 8፣ የኬንያ መንግስት ባላቸው ተካፋይነት/ሃላፊነት አምስት ግለሰቦችን በሽብርተኝነት ክስ መስርቶባቸዋል።

***ዘመቻ «ኡሳላማ ጥበቃ»:-*** እ.ኤ.አ. በአፕሪል 2014 ዓ.ም.፣ የኬንያ መንግስት፣ በኬንያ የሚገኙ የአል-ሻባብ ሽብርተኞችን እና ተባባሪዎቻቸውን/ደጋፊዎቻቸውን ለመለየትና ለማሰር፣ የ «ኡሳላማ ዘመቻን» አንቀሳቅሷል። ዘመቻው የጀመረው በናይሮቢ በአብዛኛው ሱማሌ በሆነው የኢስትሊ መኖሪያ ሰፈር ሲሆን፣ ከዛም በዘር ሱማሌዎች ወደሚኖሩበት ሰሜን ምሥራቅ የሀገሪቱ ከፍልና አብዛኛው ሙስሊም የሆኑ ነዋሪዎች በሚገኙበት ባህር ዳርቻ መኖሪያ ሠፈሮች ተስፋፍቷል። የኬንያና ዓለም ዓቀፍ የሆኑ የሰብዓዊ መብት ጥበቃ ድርጅቶች በዘመቻው የተሳተፉ የደህንነት ባለስልጣናት ጠቅላላ ጎሳዊ እና ኃይማኖታዊ ማህበረሰባት ላይ ያነጣጠረ፣ ግፍ የሰብዓዊ መብት ገፈፋዎችን፣ የመላ ምት እስራቶችን፣ ዘረፋን፣ ህገ-ወጥ እስራቶችን፣ ማሰቃየትን፣ ግድያን እና ያለ ፍንጭ የገለሰቦች መሰወርን የመሳሰሉ ወንጀሎችን ፈጽመዋል በማለት ክስ አቅርበዋል። እ.ኤ.አ. በ ሴፕቴምበር 2015፣ ገለልተኛ የሆነው መንግስታዊ የ ኬንያ ብሔራዊ ሰብዓዊ ጥበቃ ኮሚሽን (በእንግሊዝኛ ምህጻረ-ቃሉም «KNCHR») ከ እ.ኤ.አ አፕሪል 2014 ዓ.ም. ጀምሮ፣ ቢያንስ ወደ 4000 የሚጠጉ እስራቶች እንደተፈጸሙና፣ በአብዛኛው በዘር ሱማሌ የሆኑ ግለሰቦች እንደሚገኙባቸው፣ እንዲሁም ብዙዎቹ በእስራት እያሉ ከፍተኛ ስቃይ እንደደረሰባቸው በጽሑፍ አስፍሯል። በመቶዎች የሚቆጠሩ በስተ ኋላ ከእስር ተፈትተው ከመረጃ ማጣት የተነሣ የቀረቡባቸውም ክሶች ውድቅ ተደረገዋል። የኬንያ ገለልተኛ የቸልተኝነት ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን (በእንግሊዝኛ ምህጻረ-ቃሉ «IPOA») እንዲሁም ዓለም ዓቀፍ የሰብዓዊ መብት ጥበቃ ቡድኖች በጽሁፍ እንዳቀረቡት፣ በናይሮቢ ኢስትሊ መኖሪያ አካባቢ እና በሌሎችም የሀገሪቱ አካባቢዎች የተሰማሩ የደህንነት ጥበቃ ባለስልጣናት ብዛት ያላቸው ግለሰቦች ላይ አካላዊ ጥቃት እንዳደረሱ፣ መኖሪያ ቤቶችን፣ህንጻዎችን እና ሱቆችን በጥቃት ጥሰው እንደገቡ፣ እንዲሁም ከፍተኛ መጠን ያለው ገንዘብ እንደዘረፉ ይገልጻል ። በሞምባሳ፣ በጣም ታዋቂ የሆኑ አክራሪ እስልምና የኃይማኖት መሪዎች ተገድለዋል፤ ተጠርጣሪዎቹም

የኬንያ የደህንነት ጥበቃ ባለሥልጣናት ናቸው። በተጨማሪም በሞምባሳ፣ በአክራሪነት የተከሰሱ መስጊዶች ተዘግተው ከዛም ብዙ ሣይቆይ እንደገና ተክፍተዋል።

«ዘመቻ ኡሳላማ ጥበቃ» በተጨማሪም ከ ካኩማ እና ዳዳብ የስደተኛ መጠለያ ጣቢያዎች ውጪ የሚኖሩ ሁሉ የሱማሌ ስደተኞች ወደየጣቢያዎቻቸው በፍጥነት እንዲመለሱ ትዕዛዝ አስተላልፏል። ከጋሪሳ ዩኒቨርሲቲ የሽብር ጥቃት በኋላ፣ መንግስት የ ዳዳብ የስደተኞች መጠለያ ጣቢያን ለመዝጋት እና የሱማሌ ዜግነት ያላቸውን ስደተኞች ሁሉ ወደ ሀገራቸው የመመለስ ዕቅድ እንዳወጣ አስታውቆ ነበር። በፈቃደኝነት ወደ ሀገራቸው የመመለስ መርሀ ግብርም እ.ኤ.አ. በ ኦገስት 2015 ተጀምሯል።

***የሰብዓዊ መብት ጥበቃ ድርጅቶች ላይ ማነጣጠር፦*** በ እ.ኤ.አ. አፕሪል 8፣ የ ጋሪሳ ዩኒቨርሲቲ ጥቃትን ተከትሎ ፣ መንግሥት የተለያዩ ግለሰቦችን፣ ንግዶችን፣ እንዲሁም ድርጅቶችን ከአሸባሪ ቡድኖች ጋር የተያያዙ አካላት ናቸው በማለት በመመደብ የባንክ ሒሳባቸው እንዳይንቀሳቀስ ወስኖባቸዋል። ሙስሊሞች ለ ሰብዓዊ መብቶች (በእንግሊዝኛ ምህጻረ-ቃሉ «MUHURI» ተብሎ የሚታወቀው) እና «HAKI» አፍሪካ በተጨማሪ በዚህ ዝርዝር ውስጥ ተካትተዋል ። እነዚህ ሁለት ወደብ አካባቢ የሚገኙ የሰብዓዊ መብት ጥበቃ ድርጅቶች ከትክክለኛ የፍርድ ሂደት ውጪ በመንግስት የደህንነት ጥበቃ አካላት፣ በሽብርተኝነት የሚጠረጠሩ ግለሰቦች ላይ የሚፈጸሙ ግድያዎችን እና ያለ መገኛ መጥፋት ክስተቶችን የሚመዘግብ እና ኃላፊነት እንዲወሰድ ግፊትን የሚያደርጉ ድርጅቶች ናቸው። ድርጅቶቹ የመንግሥትን ድርጊቶች ተቃውመው የነበረ ሲሆን እ.ኤ.አ. በ ኖቬምበር 12 የፍርድ ቤት ዳኛ ሁለቱንም ቡድኖች ከአሸባሪነት ጋር የተያያዘ ግንኙነት እንደሌላቸው በማረጋገጥ፣ መንግስት ማስረጃ ማቅረብ ስላልቻለ፣ አሰናብቷቸዋል። ነገር ግን፣ መንግሥት የባንክ ሒሳባቸውን እስከ አሁን ድረስ እንዲያንቀሳቅሱ አልፈቀደላቸውም ፣ ይህም ድርጅቶቹ ሥራቸውን መቀጠል እንዳይችሉ አድርጓቸዋል።

ኃይማኖታዊ ድርጅቶችን መቆጣጠር፦ እ.ኤ.አ. በ ጃኑዋሪ 2016 ዓ.ም. የኬንያ መንግሥት የኃይማኖታዊ ማህበረሰቦችና መሪዎች እንዲመዘገቡ የሚያዝዝ መጠይቅ ለማስፈጸም ሞክሮ ነበር። የወጣው ህግ ኃይማኖታዊ ድርጅቶች ለመንግሥት የእምነት መግለጫ እንዲሰጡና የገቢ ምንጮቻቸውን እንዲዘረዝሩ፣ እንዲሁም የኃይማኖት መሪዎች የፖሊስ ምርመራን እንዲያልፉ፣ ተቀባይነት ካለው ኃይማኖታዊ ትምህርት ቤት የዕውቅና ማስረጃ እንዲያቀርቡ፣ እንዱሁም ከሀገር ውጪ ለሚመጡ የኃይማኖት መሪዎች የሥራ ፈቃድ እንዲያወጡና ከመኖሪያ ሀገሮቻቸው የመንግስት ድጋፍ ደብዳቤ እንዲያወጡ ያስገድዳል። እ.ኤ.አ. በጃኑዋሪ 28፣ የ ኬንያ መንግስት ወንጌላዊ ክርስትያኖች እና የሙስሊም ቡድኖች ተቃውሞ ካሰሙ በኋላ፣ ረቂቁን ከፓርላማ አስወጥቶታል

# ኢትዮጵያ

***መንደርደሪያ፦*** ኢትዮጵያ ረጅም የሆን የኃይማኖታዊ መቻቻልና ውስጠ-ኃይማኖታዊ ትብብር ሲኖራት፣ ህገ-መንግስቷም የኃይማኖት ነጻነትን ወይም እምነትን አስመልክቶ ከለላ ይሰጣል፣ እንዲሁም ኃይማኖትና መንግስት እንዲለያዩ አቅራቦት ያደርጋል። ሆኖም እ.ኤ.አ. ከ 2011-2012 ዓ.ም. ባለው ጊዜ፣ እያደገ ስለመጣው አክራሪነት ለተነሣው ጭንቀት ምላሽ ለምስጠት ሲል፣ በሀገሪቱ እስልምና ማህበረሰብ ላይ፣ የኢማሞች ሥልጠናን ጨምሮ፣ በ አል-አህባሽ የእስልምና ትርጉም እንዲመሩ ጫና ጥሏል፤ በማህበረሰቡራስን መቻል ሥልጣን/ነጻነት ላይ እና በኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ከፍተኛ ምክር ቤት

(በእንግሊዝኛ ምህጻረ-ቃሉ «EIASC» ተብሎ በሚታወቀው አካል ላይ) ጣልቃ ገብቷል፤ ከዛም እነዚህን ድርጊቶች የሚቃወሙና ሠላማዊ የተቃወሞ ሠልፍ ያደረጉ ሙስሊሞችን አስሮ ፍርድ ቤት አቅርቧል።

***ለሰላማዊ ተቃውሞዎች የተሰጡ ብይኖች፡-*** እ.ኤ.አ. በ ጁላይ 6 እና ኦገስት 3/ 2015 ዓ.ም. በተከታታይ ሁኔታ፣ የኢትዮጵያ መንግሥት 18 ያህል እ.ኤ.አ. 2012 ሙስሊም ተቃውሞ እንቅስቃሴ መሪዎችን ወንጀለኝነታቸው ተረጋግጦ ፍርድ አስተላልፎባቸዋል። እነሱም ወንጀለኛ ሆነው የተገኙት እስላማዊ መንግስትን ለመመስረት በሚል ሲሆን ከ ሰባት እስከ 22 ዓመታት በእስራት እንዲቀጡ በአከራካሪው የኢትዮጵያ ጸረ-ሽብርተኝነት አዋጅ መሠረት ተወስኖባቸዋል። የአሜሪካ መንግሥት ባለሥልጣናት እና የሰብዓዊ መብት ጥበቃ ድርጅቶች የኢትዮጵያ መንግሥት የጸረ-ሽብርተኝነት አዋጁን በመጠቀም እንከን አውጪዎች/ተቃዋሚዎችን ጸጥ አሰኝቷል በማለት ተችተዋል። እ.ኤ.አ. በ ሴፕቴምበር 16፣ ወንጀለኛ ተብለው ከተገኙት መካከል ለስድስቱ የኢትዮጵያ መንግሥት ምህረት አድርጓል።

***የጨመረ «EIASC» የመስጊዶች ቁጥጥር፡-*** የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ከፍተኛ ምክር ቤት የሙስሊም ማህበረሰቡ ተወካይ አካል ነው፣ ነገር ግን እ.ኤ.አ. በ 2011 ዓ.ም. ከተደረገው የመንግሥት ጣልቃ ገብነት የተነሣ፣ ብዙ የማህበረሰቡ አባላት አይደግፉትም አባላቱንም የመንግሥት ተወካይ መሪዎች ብለው ያዩዋቸዋል። በዚህም ሪፖርት ማቅረቢያ ወቅት «EIASC» የሙስሊም ማህበረሰቡ ላይ ያለውን ማስተዳደር ጨምሯል። ሁለት መመሪያዎችን በማውጣት ከፍ ያለ ቁጥጥር፣እና አልፎም የኢትዮጵያ መስጊዶች ላይ ባለቤትነት እንዲሰጡት አድርጓል። መመሪያዎቹ የመስጊዶች አስተዳደርን አስመልክቶ ዝርዝር ህግጋትን ያጠቃልላሉ፤ ለ «EIASC» ለመስጊዶች ውስጣዊ መተዳደሪያዎችን እንዲሰጥና የመስጊዶች ተቀጣሪዎችን እንዲመርጥ ሥልጣን ይሰጣሉ፤ እንዲሁም ከ «EIASC» በጽሁፍ የቀረበ ፈቃድ ውጪ ህዝባዊ ስብሰባዎችን፣ ንግግሮችንና ስብከቶችን፣ እንዲሁም ገንዘብ ማሰባሰቢያ ዝግጅቶችን ይከለክላል።